የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ ጥር ፲፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 15
ADDIS ABABA, 27th January, 2016

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለብሔራዊ የኃይል አቅርቦት መቆጣጠሪያ ማዕከል ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …………ገጽ ፱ሺ፭፻፳፫

## CONTENT

PROCLAMATION No. 991/2016

agence Franciase De Development (AFD) Credit Facility Agreement for financing of the National Load Dispatch Center Project Ratification Proclamation ………….page 9523

አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፩/፪ሺ፰ ዓ.ም

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለብሔራዊ የኃይል አቅርቦት መቆጣጠሪያ ማዕከል ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፵ ሚሊዮን ዩሮ (አርባ ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘውን የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፲፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

PROCLAMATION No. 991/2016

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT FACILITY AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND AGENCE FRANCAISE DE DEVELOPMENT (AFD)**

**WHEREAS,** a Credit facility Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agence Franciase De Development (AFD) stipulates to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit Facility in an amount of 40,000,000 EURO (forty million EURO) for financing the National Load Dispatch Center Project was signed in Addis Ababa on 28th day of July, 2006;

**WHEREAS,** the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Facility Agreement at its session held on 27th the day of 2016.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ " ለብሔራዊ የኃይል አቅርቦት መቆጣጠሪያ ማዕከል ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፺፩ /፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **<u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በፈረንሳይ የልማት ኤጀነሲ መካከል ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተረፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 1048 01 W በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፵ ሚሊዮን ዩሮ (አርባ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፲፱ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "agence Franciase De Development (AFD) Credit Facility Agreement for financing of the National Load Dispatch Center Project Ratification Proclamation No. 991/2016."

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Credit Facility Agreement Number 104801 W signed in Addis Ababa on the 28th day of July, 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agence Franciase De Development (AFD) is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit facility among amount of 40,000,000 EURO (forty million EURO) in accordance with the terms and conditions set forth in Credit Facility Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 27th day of January,2016**

**MULATU TECHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**